# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 22 ታህሳስ 2 ቀን 2012 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ሕገ መንግሥቱና የለውጡ ሂደት



# ታህሳስ 5 ቀን 2012 ዓ.ም ምሽት በኢንተርኮንቲነንታል ሆቴል

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ታህሳስ 5 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት የሚጀምር የገቢ ማሰባሰቢያ የእራት ግብዣ በኢንተርኮንቲነንታል ሆቴል አዘጋጅቷል። በዚህ እራት ግብዣ ላይ መገኘት ከገቢ ማሰባሰቢያነቱ በተጨማሪ በርካታ ተጓዳኝ ጠቀሜታዎች አሉት ብሎ ፓርቲያችን ያምናል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕዝብ መፈተሽ ያለባቸው በምርጫ መግለጫዎቻቸው (ማኒፌስቶዎቻቸው) እና በምርጫ ወቅት ቅስቀሳዎቻቸው ብቻ አይደለም። በምርጫዎች መካከል ፓርቲዎች ምን ሲሠሩ እንደቆዩ፤ ለወደፊቱስ ምን ለመሥራት እንዳቀዱ መራጮች ማወቅ ይፈልጋሉ። በመደበኛ ስብሰባዎች ወቅት ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ላይሆን ይችላል፤ የእራት ምሽቶች ግን ለእንደዚህ ዓይነት ውይይቶች የተመቹ ናቸው።
በዚህ የእራት ግብዣ ላይ መገኘትዎ ኢዜማን ከማጠናከር በተጨማሪ ስለኢዜማ አባላት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ይረዳዎታል። አጋጣሚውን ለኢዜማ መሪዎችና አባላት ማሳወቅ የሚፈልጉትን መልዕክት፣ ጥቆማ ወይም አስተያየት ካለ ለመስጠት አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።
የኢዜማ እራቶች ምግብ ብቻ የሚበላባቸው መደበኛ እራቶች አይደሉም። የኢዜማ እራቶች ኢትዮጵያዊያን ስለሀገርና ወገን ደህንነት የሚወያዩባቸው፤ ለኢትዮጵያ ተመሳሳይ ህልም ያላቸው ወገኖች እርስ በርስ የሚተዋወቁባቸውና የግንኙነት መስመሮቻቸውን የሚያጠብቁባቸውና የሚመክሩባቸው መድረኮች ናቸው።

ኢዜማ ከተመሠረተበት ጊዜ አንፃር ሲታይ እስካሁን ያከናወናቸው ተግባራት አበረታች ናቸው። በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉት 547 የምርጫ ወረዳዎች ውስጥ በ400ዎቹ መዋቅር ተዘርግቷል፤ ከእነዚህ ውስጥ 214ቱ የየራሳቸውን ጽ/ቤቶች ከፍተዋል። ይህ መልካም ውጤት ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። ዕቅዳችን ሁሉንም የምርጫ ወረዳዎች ማዳረስ ነው። በየምርጫ ወረዳዎች መዋቅር መዘርጋትና ቢሮ መክፈት ብቻውን ስኬት አይደለም። በእያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ ውስጥ ጠንካራ ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረን ማድረግ ይጠበቅብናል። ከዚህም በተጨማሪ ከእያንዳንዱ የምርጫ ወረዳ የወረዳውን ችግር የሚረዱ፣ የአካባቢውን ባህል ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ በወረዳው ማኅበረሰብ ዘንድ ከበሬታ ያተረፉ ብዙ አባላትን እና እጩዎችን ማፍራት ይኖርብናል። ይህ ከፍተኛ ሥራ ይጠይቃል፤ በእርስዎ እርዳታ ኢዜማ ይህንን ተግባራዊ ያደርጋል።

እስካሁን ከ100 በላይ እውቅ የሀገራችን ምሁራን የተሳተፉባቸው 18 የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። ተጨማሪ የፖሊሲ ሰነዶች በዝግጅት ላይ ናቸው። ኢዜማ ለሀገራችን የሚበጁትን የፖሊሲ አማራጮችን በተሟላ መንገድ የማዘጋጀት እቅድ አለው። የኢዜማን ፕሮግራም እና ፖሊሲ ዶክመንቶች በሙሉ ከአማርኛ በተጨማሪ በተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎች ለማቅረብ እየተንቀሳቀስን ነው። የእርስዎ ዕርዳታ ከታከለበት ይህ ተግባራዊ ይደረጋል።
በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊን በሀገራቸው ፖለቲካ ላይ የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው እስካሁን በ32 የዓለም ከተሞች የድጋፍ ማኅበሮች ተቋቁመዋል። ይህ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡

በመጪው ምርጫ ኢዜማን ወክለው ለሚወዳደሩ እጩዎች በሙሉ ወጥ የሆነ ሁሉን-አቀፍ ስልጠና ለመስጠት ዕቅዱ ተጠናቋል። ምርጫውን በምርጫ ድምጽ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ስነምግባር ማሸነፍ ይኖርብናል። ይህ ከፍተኛ ስልጠና ይፈልጋል። የእርስዎ እርዳታ ከታከለበት ተግባራዊ ይሆናል።
ወደ እራት ግብዣችን ሲመጡ ስለ እነዚህና ሌሎች እቅዶቻችን ይሰማሉ። በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በሀሳብ በመደገፍ የዜጎች ሉዓላዊነት የተረጋገጠባት እውነተኛ ፌደራላዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትኖረን የሚታገለውን ኢዜማ ይርዱ።
ታህሳስ 5 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በኢንተርኮንቲነንታል ሆቴል እንገናኝ ።




# አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ታህሳስ 2 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ሕገ መንግሥቱና የለውጡ ሂደት

የወያኔ ሥርዓት በሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረትና የዘር መድሎን ለመቃወም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ ዓይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። እነኝህ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሰላማዊ መንገድ፤ ሌላ ጊዜ በሕዝባዊ እምቢተኝነት አንዳንዴም በነፍጥ በታገዘ የትግል ሂደት ሲካሄዱ ቆይተዋል። ሥርዓቱም እነኝህን ተቃውሞዎች ለማፈን አንዳንዴ በጥቅም በመደለል፤ ሌላ ጊዜ ፍጹም ገደብ የሌለው ጉልበት በመጠቀም የሥልጣን ጊዜውን ለማራዘም ማድረግ የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። በዚህም መልክ ለ27 ዓመታት ዘልቋል። በተለይ የወያኔ ፍጹም የሥልጣን የበላይነት በእነኝህ ትግሎች ግፊትና በኢሕአዴግ ውስጥ በተደረገ የውስጥ ትግል እስካበቃበት ጊዜ ድረስ በነበሩት ሶስት ዓመታት ጊዜ የወያኔን ሥርዓት የሚቃወሙት ኃይሎች ያደረጓቸው ቀጣይነት ያላቸው የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎች ሥርዓቱ እንደወትሮው በማባበልም ሆነ በጉልበት ሊያቆማቸው የማይችሉበት ደረጃ ላይ አድርሰውት ነበር። ሥርዓቱ በፍጹም እንደወትሮው ለመግዛት የማይችልበት ደረጃ ላይ እንደደረሰና ሀገሪቱም አደገኛ ወደሆነ ቀውስ እየገባች መሆኑ ግልጽ ሲሆን፣ ለውጥ ግድ መሆኑ ግልጽ የሆነላቸው በኢሕአዴግ ውስጥ ያሉ “የለውጥ ኃይሎች” ቀውሱን ለማስቆምና ከቁጥጥር ውጭ ከመውጣቱ በፊት ሀገሪቱን ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተረጋጋና ለዘብተኛ በሆነ የለውጥ ሂደት (ሪፎርም) እናሸጋግረዋለን በሚል ቃልኪዳን የመንግሥትን ሥልጣን ተረከበው፤ ሌሎችን ከኢሕአዴግ ውጭ ያሉ የለውጥ ፈላጊዎች በዚህ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ጠርተውና በውጭ ሀገር የነበሩትን ተቃዋሚዎች ወደ ሀገር ገብተው በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እንቅስቃሴያቸውን እንዲያደርጉ ጋብዘው፤ በእስር ላይ የነበሩትንም “በምህረት” በመልቀቅ በታላቅ ተስፋ ነበር የለውጥ ሂደቱ የተጀመረው።

እነኝህ ከኢህአዴግ ውስጥ የወጡት የለውጥ ኃይሎች የሚያካሂዱትን የለውጥ ሂደት በተቻለ መጠን፤ ቢያንስ በነሱ እምነት፤ በሀገሪቱ ውስጥ ባለውና በወያኔ ሥርዓት በጸደቀው የሕገ መንግሥት ማእቀፍ ውስጥ ሆነው እንደሚያደርጉት ነው የሚያምኑት። ይህን የሚያደርጉት ግን ሕገ መንግሥቱ ፍጹም ትክክል ነው ወይንም በትክክል ሲተገበር ነበር በሚል እምነት ሳይሆን (ቢያንስ ሕገ መንግሥቱ በብዙ መልኩ በኢሕአዴግ በራሱ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳልነበር፤ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ውጭ የተደረጉት የውሸት ምርጫዎች በጊዜው የነበረውን መንግሥት ህዝባዊ ተቀባይነት እንዳላላበሰው ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ ለዚህም ነው ለውጥ እንደሚያስፈልግ ያመኑት) ይህንን የለውጥ ሂደት ለመምራት የመንግሥት ስልጣንን የያዙት በዚሁ ሕገ መንግሥት ስም ስለሆነ ከዚያ ውጭ ለመሥራት የሚችሉበት የተቀባይነት መሰረት (legitimacy) እንደሌላቸው ስለሚያውቁ ነው። ያም ሆኖ ግን ሀገሪቱ ከገባችበት ችግር አንጻርና ብዙሀኑ ሕዝብ ከሚጠይቀው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምስረታ አንጻር በሰላማዊ መንገድ በሚደረጉ ውይይቶችና ተቋማዊ ለውጦች ሕገ መንግሥቱን ብዙ ሳይነካኩ ቀስ በቀስ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር ይቻላል ብለው፤ በተለይ በለውጡ ጅማሬ ወራት፤ እንደሚያምኑ ግልጽ ነበር።

በሌላ በኩል ከኢሕአዴግ ውጭ ያለው በተለያየ መንገድ ለለውጥ ሲታገል የነበረው ኃይል የወያኔን የበላይነት ከማክሰም ባሻገር እንዲመጣ የሚፈልገው ለውጥ ምን እንደሆነ ሙሉ ስምምነት እንዳልነበረው ግልጽ ነው። በዚህ የትግል ወቅት በጉልህ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የተለያዩ የተደራጁ ኃይሎች ያላቸው የተለያየ የፖለቲካ ፕሮግራም፤ በየጊዜው በነኝህ ኃይሎች ውስጥ ይስተዋሉ በነበሩ የከረሩ የቃላት ግጭቶች ሙሉ ስምምነት እንዳልነበር ምስክር ናቸው። ከዚህም ውጭ በተለይ በመጨረሻዎቹ ሶስት አመታት በተደረጉት የለውጥ እንቅስቃሴዎች በንቃት ሲሳተፉ የነበሩ የተለያየ ክልል ወጣቶች፤ በራሳቸውም ሆነ ከኋላ በሚገፏቸው የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች አማካኝነት ኢ-መደበኛ በሆነ አደረጃጀት ባብዛኛው በየክልሎቹ ተወስነው፤ አንዳንዴም በስሱ በመናበብ ሲንቀሳቀሱ፤ የወያኔን የበላይነት ከመስበርና ቢቻላቸውም ባጠቃላይ የኢሕአዴግን ሥልጣን ከማስወገድ ውጭ በምትኩ እንዲፈጠር በሚፈልጉት ሥርዓት ዙሪያ ይህ ነው የሚባል የጋራ ግንዛቤ ነበራቸው ለማለት ያዳግታል።

በእርግጥ ሁሉም የተቃውሞ ኃይሎች በምትኩ የሚፈጠረው ሥርዓት “ዴሞክራሲያዊ” መሆን አለበት ብለው እንደሚያምኑ በየጊዜው ቢገልጹም ይህ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገሪቱ ሁኔታ ምን መምሰል እንዳለበት፤ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ላይ የግድ መከበር ያለባቸው መሠረታዊ መርሆዎች የትኞቹ እንደሆኑ፤ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን የሚያስፈልገው የፖለቲካ ባህል ዙሪያ...ወዘተ አይደለም የጋራ ግንዛቤ ሊኖራቸው በተረጋጋና በሰለጠነ መንፈስ ውይይት ለማድረግ እንኳን ሳይችሉ ነው ይህ የለውጥ ሂደት የተጀመረው። በዚህ ለውጥ ፈላጊ ኃይላት መሀከል ያሉት ልዩነቶች ምንጫቸው የተለያየ ቢሆንም የለውጥ ሂደቱ ገና ከመጀመሩ በፊት ውስጥ ለውስጥ ሲፋፋ የነበረውና ለውጡም ገና እንደተጀመረ ፍንትው ብሎ ባደባባይ የወጣው መሠረታዊ ልዩነት በወያኔ ሥርዓት በጸደቀው ሕገ መንግሥት ላይ ያለው ልዩነት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው ልዩነት በአሁኑ ጊዜ ከኢሕአዴግ ውጭ ባለው የለውጥ ኃይሎች

መሀከል ብቻ ሳይሆን በኢሕአዴግ ውስጥም መሰረታዊ የልዩነት ምክንያት እየሆነ ስለመጣ በተወሰነ ሁኔታ ከለውጡ በፊት የነበረውን የኃይል አሰላለፍም ክፉኛ እየፐወዘው ይገኛል። ይህ ልዩነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አሁን በሀገራችን ባሉት የተለያዩ ግጭቶች ውስጥም እየተንጸባረቀ እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህም እነኝህን ከሕገ መንግሥት ጋር የተያያዙ የጊዜው ችግሮች ጥራት ባለው መንገድ መረዳትና በማኅበረሰባችን ውስጥ የሰከነ ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ስናደርግ ግን ሁለት ነገሮች እንዳይሳከሩ ውይይቱን በጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቀናል። እነኝህም፤

1. ባጠቃላይ አሁን ባለው ሕገ መንግሥት ዙሪያና ሀገራችን ዘላቂ የሆነ የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት የሚያስችላት ምን ዓይነት ሕገ መንግሥት ነው? በሚለው ዙሪያ በባለሙያዎች የታገዘና ማኅበረሰቡን በሰፊው ያሳተፈ የሰከነ ውይይት የሚደረግበትና ዘላቂና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመስረት የሚመቸንን ሕገ መንግሥት በአዲስ መልክ ወይንም አሁን ያለውን ለማሻሻል የምንሄድበት ሂደት፤
2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው የውይይት ሂደት ተደርጎ ብዙሀኑ የሚስማማበትና በማኅበረሰቡ ሙሉና የነቃ ተሳትፎ፤ በመጨረሻም በሕዝበ ውሳኔ (ሪፈረንደም) የሚጸድቅ ሕገ መንግሥት እስከሚኖረን ድረስ አሁን ባለንበት የሽግግር ሂደት ውስጥ እየገጠሙን ያሉትን ከሕገ መንግሥቱ ጋር የተያያዙ ችግሮች በምን መልክ ብንሄድባቸው ነው የሽግግር ሂደቱ እንዳይሰናከል ማድረግ የምንችለው የሚለው ውይይት ነው።

በዚህ ጽሑፍ ላይ ሕገ መንግሥቱን እንደ አንድ የፖለቲካ ሥርዓት መመሥረቻ ሰነድ ከሕግና ከፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ አንጻር በዝርዝር ለመተቸት አልታሰበም። ይህን አስፈላጊ ሥራ ወደፊት በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ምክንያታዊና የሰለጠነ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ እንመለስበታለን። በዚህ ጽሑፍ ላይ በተለየ ለማተኮር የታሠበው፤ በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ከላይ የተባለውን ዓይነት የሰለጠነ ውይይት ከመደረጉ በፊት፤ ከሕገ መንግሥቱ ጋር በተያያዙ የሚነሱትና ለግጭቶች ምክንያት የሆኑት ችግሮች፤ የተጀመረውን ለውጥ እንዳያደናቅፉና ሀገሪቱን ወደ ከፋ ብጥብጥ እንዳይወስዳት በምን ዓይነት ብልሀት ብናልፍ ይሻላል? የሚለውን እጅግ አንገብጋቢ የሆነው የጊዜው ጥያቄ ላይ አጭር አስተያየት ለመስጠት ነው። ወደ መፍትሄ ሀሳቡ ከመሄዳችን በፊት ግን የችግሩን ዓይነትና ውስብስብነት በጠራ መልኩ በመጀመሪያ ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግ በሚቀጥለው ክፍል ይህንን ባጭሩ እንዳስሳለን። ለዚህ ውይይት እንዲረዳ በመጀመሪያ ሕገ መንግሥቱን በጥቅሉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ለይቶ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው፣ ይህ ሕገ መንግሥት ለሁሉም ዜጎች እንደ ዜጋ ያጎናጸፋቸው መሠረታዊ መብቶችና በዚህ ላይ በመመሥረት በመንግሥት ምሥረታ ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎና ወሳኝነት የሚገልጽበት አካል ነው። እነኝህ ከሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችና ከዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጋር በተያያዘ የተደነገጉት መብቶች በመርህ ደረጃ ብዙ መሰረታዊ ክርክር የማይነሳባቸው ግን በፍጹም በስራ ላይ ያልዋሉ የሕገ መንግሥቱ ክፍሎች ናቸው።

ሁለተኛው ክፍል፣ ሕገ መንግሥቱ "ብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝቦች" ለሚላቸውና እያንዳንዳቸውን የተለየ የሚያደርጋቸውን መስፈርት፤ ወይንም እነኝህ ምደባዎች በሚሰጡት የወል መብቶች ላይ ምንም ልዩነት ሳያስቀምጥ በጥቅሉ የዚህ የወል መብት ተጠቃሚ የሆኑ አካላት አንድ የጋራ የሚግባቡበት ቋንቋና የራሳቸው ባህል እንዲሁም የስነ ልቦና ትሥሥር ያላቸውን ማንነቶች መሆኑን በጥቅሉ የሚገልጸው ክፍል ነው። ለነኝህ ለሁሉም የወል ስብስቦች የሚሰጣቸው ከራስ ማስተዳደር ጋር የተያያዙና እስከ መገንጠል ድረስ የተለጠጡ መብቶች፤ እንዲሁም እነኝህ መብቶች ይገባቸዋል ተብሎ የተጠቀሱት የወል ስብስቦች የተወሰኑበት አግባብ ነው። ባብዛኛው ከሕገ መንግሥቱ ጋር በተያያዘ የሚነሱት ልዩነቶች ከዚህ ከሁለተኛው የሕገ መንግሥቱ ክፍል ጋር የተያያዙ ናቸው። ከእነኝህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በሀገራችን ያሉትን የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች በጥቅሉ በ3 መደብ ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ እነኝህም፤

1. ሕገ መንግሥቱ ውስጥ የተቀመጡት አንቀጾች በሙሉ ከሞላ ጎደል ትክክልና ተገቢ (ያው በትክክል ካለመፈጸማቸው በቀር) ናቸው ስለዚህም መቀጠል ያለባቸው ናቸው፤ በተለይ ከቡድን መብት ጋር የተያያዙት አንቀጾች በምንም ዓይነት ሊነኩ አይገባም፤ መስተካከል ያለበት እነኝህን መብቶች በትክክልና ያለምንም መሸራረፍ መተግበር እንዲቻል ማድረግ ነው፤ ይህ ካልሆነ እነኝህ "ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች" በአንድ ሀገራዊ ጥላ ስር ሊቀጥሉ አይችሉም፤ ስለዚህም ሀገሪቷን ሊበታትኗት ይችላሉ የሚል አመለካከት ያለው ኃይል ነው።
2. ሁለተኛው አመለካከት ከዚህ በተቃራኒው ሄዶ የሀገሪቱ ችግሮች ሁሉ ምንጭ ይህ ሕገ መንግሥት፤ በተለይም ደግሞ ከወል መብቶች ጋር በተያያዘ የሚደነግገው ክፍል ነው። ይህ ደግሞ በመርህ ደረጃም ሆነ ባተገባበር ሂደት በጣም ብዙ ችግሮችና መዘዞች ያሉት ክፍል ነው። ይህ ክፍል ሙሉ ለሙሉ ካልተቀየረ ወይንም ካልተሻሻለ በቀር አይደለም ዘላቂ ሰላም ይህ ነው የሚባል ተአማኒነት ያለው ምርጫ እንኳን ማድረግ አይቻልም፤ ሀገሪቱም እንደ ሀገር ለመቀጠል አትችልም የሚለው አመለካከት ነው።
3. ሶስተኛው አመለካከት በነኝህ መሀከል ያለውና ሕገ መንግሥቱ ጥሩ ነገሮች ያሉትን ያክል (በተለይ የመጀመሪያው ዜጎችን በሚመለከት ያሉት ድንጋጌዎች)፤ በጣም ብዙ ግልጽነት የጎደላቸውና በተግባር ለመተግበር እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ፤ ከዚያም አልፎ የሀገሪቱን ህልውና የሚፈታተኑ አንቀጾች ስላሉት በነኛ ላይ ምክንያታዊ በሆነና ለዘላቂው የሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ቅድሚያ በሚሰጥ፤ በፖለቲካ ኃይሎችና በማኅበረሰቡ ውስጥ ውይይት ተደርጎ የሚሻሻሉት እንዲሻሻሉ ማድረግ ይሻላል የሚለው አመለካከት ነው።

እነኝህ በጥቅል የተቀመጡ ልዩነቶች በውስጣቸው ብዙ ዝርዝር አከራካሪ የሆኑ ከመርህም ካተገባበርም ጋር የተጎዳኙ ጉዳዮች አላቸው። እነኝህ ልዩነቶች በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መሀከል ያሉ ልዩነቶች ብቻ ሳይሆኑ በራሱ በገዥው ፓርቲ መሀከል፤ በተቃዋሚ ኃይሎች መሀከል፤ በተወሰነ ደረጃም ከፓርቲዎች ውጭም ባሉ የሲቪክ ማኅበረሰብና ምሁራንም መሀከል ያሉ ሰፊ ልዩነቶች ናቸው። እነኝህ ልዩነቶች ሁሌም በጠንካራ ምክንያታዊነት ላይ የተመሠረቱ ሳይሆኑ በጣም ጠንካራ በሆነ ስሜታዊነት የታጀቡ ናቸው። ከስሜታዊነትም ባሻገር በውስጣቸው "የወደፊቱን ካለማወቅ" የመጣም የውስጥ ፍርሀት ያዘሉ ናቸው። ለምክንያታዊ ውይይትም አስቸጋሪ የሚሆኑት ለዚህ ነው። በነኝህ ምክንያቶችም የለውጡን ሂደት ራሱ "ምን እንደሚያመጣ አይታወቅም" ከሚል

ፍርሃት ለውጡ ከመደላደሉ በፊት በነኝህ "ሕገ መንግሥታዊ" ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ጥያቄዎች ሕገ መንግሥቱ ከመቀየሩ ወይንም ከመሻሻሉ በፊት አሁኑኑ "መስመር ማስያዝ" የሚፈልጉ አሉ። አንዳንዶቹ ይህ ሕገ መንግሥት ሳይቀየር በፊት የሚደረግ ምንም ዓይነት የለውጥ ሂደት ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሄድ አይችልም፤ ስለዚህም ይህን ጉዳይ መጀመሪያ መፍታት አለብን ብለው ከልባቸው የሚያምኑ ናቸው።

## በሕገ መንግሥት ዙሪያ የሚደረግ ውይይት መቼ?

በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ያሉት ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው ትልቁ ውዥንብር ደግሞ ያለው እነኝህን ልዩነቶች ለማቀራረብና ለመፍታት እንዴት እንሂድባቸው? የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ላይ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው በአሁኑ ጊዜ "ሽግግሩን" እየመራው ያለው ኃይል ራሱ የቆመበት የሥልጣን መሠረት በዚህ ሕገ መንግሥት ላይ የተመሠረተ ነው ብሎ ስለሚያምን ይህን ሕገ መንግሥት "በሽግግሩ ወቅት" የመነካካት ምንም ፍላጎት የለውም። ለውጡን ከላይ ሆነው የሚዘውሩት "የለውጥ ኃይሎች" በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ብዙ ህጸጾች እንዳሉ ቢቀበሉም እንኳን አሁን ባለው ያልተረጋጋ ሁኔታ ይህን ጥያቄ ማንሳት ግጭቶችን ከማባባስ ባሻገር በደንብ የታሰበበትና ከስሜታዊ ግፊት የወጣ ሕገ መንግሥታዊ ውይይት ሊደረግ ይችላል ብለው አያምኑም። በተቃዋሚ ወገን ያሉ ኃይሎች ብቻ ሳይሆን በገዥው ፓርቲ ውስጥ ያሉ የለውጡን ሂደት በጥርጣሬና አንዳንዴም በግልጽ የሚደናቀፍ ሂደት ላይ የተሰማሩ ኃይሎችም ሕገ መንግሥቱን ባሁኑ ጊዜ መነካካት የሚፈልጉትን ለውጡን የማደናቀፍ ሥራ ለመሥራት ያመቻናል ብለው እንደሚያምኑ መገመት አያዳግትም። ከዚህ አንጻር "የለውጥ ኃይሎቹ" ሕገ መንግሥቱን ባሁኑ ጊዜ ለውይይት ላለመክፈት የሚፈሩበት ሁኔታ ምክንያታዊ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ደግሞ ዝም ብሎ በግምት የተሰነዘረ ሳይሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመጀመሪያ ላይ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት ያቀረቡት ጥቅል የሆነ የለውጥ ሂደቱ ፍኖተ ካርታ የሚያንጸባርቀው ይህንን ነው። በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ፍኖተ ካርታ ሶስት ደረጃ ያለውን የለውጥ ወይንም "የሽግግር ሂደት" እንደሚከተለው አስቀምጠውታል፤

1. በመጀመሪያ በሀገሪቱ በሙሉ ሰላም ማምጣትና ማኅበረሰቡን ማረጋጋት፤ ለሰከነ ውይይት የሚሆን የሰላም ድባብ በሀገሪቱ ሁሉ እንዲሰፍን ማድረግ
2. በሁለተኛው ደረጃ እውነተኛ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ለማድረግና የማኅበረሰቡን እውነተኛ ፍላጎት ለማየት እንዲቻል የሚያስፈልጉትን የሕግና የተቋማት ለውጥ (ሪፎርም) ማድረግና ለመጪው ምርጫ ማዘጋጀት። ምርጫው ምንም ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የማይችል የህዝብ ነጻ ስሜት የተረጋገጠበት እንዲሆንና በእርግጥም በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝብ ፍላጎት የተንጸባረቀበት መንግሥት መመሥረት፤
3. እነኝህ በሕዝብ ነጻ ምርጫ የተመረጡ የመንግሥት አካላት ከሲቪክ ማኅበረሰቡና ከሀገሪቱ ምሁራን ጋር በመሆን በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ጥናቶችን አጥንቶ ሰፊና ሕዝቡን ያሳተፉ ተከታታይ ውይይቶች በማድረግ በሚዘጋጅና በመላው ሕዝብ ውሳኔ በሚጸድቅ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ የሀገሪቱን ዘላቂ የፖለቲካ ሥርዓት ማዘጋጀት።

ይህ ከሀገሪቱ ሁኔታ አንጻር ምክንያታዊ የሆነ አካሄድ በከፊልም ቢሆን ተቀባይነት ካለው በሕገ መንግሥት ዙሪያ የሚደረገው ውይይት መቼ መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ በጥቅሉ ይመልሰዋል። በሕገ መንግሥቱ ዙሪያ ያሉትንና ከላይ የተጠቀሱትን ልዩነቶች ግን አይደለም መፍታት ምንም አይነካቸውም። ከለውጥ ሂደቱ አካሄድ አንጻር ይህ ፍኖተ ካርታ የማይመልሰው ወሳኝ ጥያቄ ግን ይህ ውይይት ተካሂዶ አብዛኛው ሕዝብ የተቀበለው በተረጋጋ ውይይት ላይ የተመሰረተ ሕገ መንግሥት እስከሚኖረን ጊዜና በተለይም ምርጫው ተካሂዶ እስከሚጠናቀቅ ጊዜ ድረስ ከሕገ መንግሥት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች የለውጥ ሂደቱን በማያደናቅፉበት ሁኔታ በምን መልክ እንመልሳቸዋለን? የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ለገጠሙን የተለያዩ ግጭቶችና ከላይ በፍኖተ ካርታው ላይ በአንደኛና በሁለተኛው ደረጃ የተጠቀሱትን የለውጥ ሂደት ደረጃዎች በሰላምና በተረጋጋ ሁኔታ እንዳይሻገራቸው ከፍተኛ ፈተና ውስጥ የከተቱት ጥያቄዎች ናቸው።

ለምሳሌ በደቡብ ክልል ከሰሞኑ የተፈጠሩት አስከፊ ግጭቶች ከዚህ ጥያቄ ጋር በቀጥታ የተገናኙ ናቸው። የሲዳማ ዞን ለብቻዬ ክልል መሆን እፈልጋለሁ የሚለው ጥያቄና ይህ ጥያቄ በተገቢው ፍጥነት አልተመለሰልኝም በሚል የተፈጠረው ግጭት (ጥያቄው የተጠየቀበትን ያካሄድ አግባብ ለጊዜው ትተን) "ሕገ መንግሥቱ የሰጠኝን መብት ተነፍጊያለሁ" የሚል ቅሬታን ያዘለ ነው። ጥያቄው አሁን ያለው ሕገ መንግሥት ተፈጻሚ ይሁንልኝ የሚል ነው። ሆኖም በደቡብ ክልል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ዞኖች (ከሲዳማ ውጭ ቢያንስ 10 ደርሰዋል) የራሳቸው የክልል እንሁን ጥያቄ አቅርበዋል። አሁን ባለው ሕገ መንግሥት እነኝህ 10 ዞኖች ብቻ ሳይሆን በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከ56 ያላነሱ "ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች" ይህ መብት እንዳላቸውና የየራሳቸውን ክልል መፍጠር እንደሚችሉ ይደነግጋል። በሌላ በኩል ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ ሀገሪቱን የከፋፈለው በዚህ ጥቅል መስፈርት ላይ ቢሆንም ሕገ መንግሥቱ ሲዋቀር በይፋ የሚያውቃቸው 9 ክልሎችን ብቻ ነው። ከነኝህ ክልሎች ውስጥ አንዳቸውም አንድ ወጥ የሆነ "ብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝብ" ብቻ ያላቸው አይደሉም። ስለዚህም ነው የምናያቸው ከዘር ጋር የተገናኙ ግጭቶች በክልሎች ውስጥም በክልሎች መሀከልም የሆነው። እንደሁኔታው አሁን በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ያሉት 9 ክልሎችም በዚህ መስፈርት ተከፋፍለው የተለያዩ ክልሎች ከውስጣቸው ሊወጡ እንደሚችሉ ይታወቃል። በሀገሪቱ ውስጥ አሉ የሚባሉት ከ84 በላይ "ብሄር፤ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች" ሁሉም የየራሳቸውን ክልል ለመመሥረት የሚከለክላቸው ምንም ነገር በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ የለም። በተለይም በነኝህ የወል ስብስቦች ውስጥ ያሉ ልሂቃን ከዚህ አይነት አከላለል እንጠቀማለን ብለው ሲያምኑ፤ ወይንም ክልሎች የራሳቸው "የጦር ኃይል" በሚያቋቁሙበት ሁኔታና የዜጎች ደህንነት የሚጠበቀው ለክልሉ ተጠሪ በሆነ ኃይል ብቻ ነው ተብሎ ሲታመን፤ ይህን "የዘውጌ ብሄረተኝነት" ስሜት ቀስቅሰው ማኅበረሰቡ ይህን ጥያቄ በስሜት እንዲያነሳ ማድረግ እንደሚችሉ (በተለይም አማራጭ ሀሳብ ያላቸውን በየክልላቸው እንዳይገቡና ሕዝቡን እንዳያስተምሩ በመከልከል ወይንም በማስፈራራት) መገመት ብቻ ሳይሆን በተግባር ያየነው ነው። መቼም ይህን ሕገ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ እንደግፋለን የሚሉት የፖለቲካ ኃይሎች እንኳን ኢትዮጵያን በዚህ ዓይነት በ84 "እስከመገንጠል ድረስ መብት ባላቸው"ና የራሳቸው የጦር ኃይል ባደራጁ "ብሄር ብሄረሰብና ሕዝቦች" ክልሎች ከፋፍሎ እውነተኛ ሰላምና ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መፍጠር ይቻላል ብለው ያስባሉ ለማለት አይቻልም። (በነገራችን ላይ ሕገመንግሥቱ

ክልሎች የራሳቸው ፖሊስ ኃይል እንዲኖራቸው እንጂ ከዚያ ያለፈ "የጦር ኃይል" እንዲያቋቁሙ አይፈቅድም። ያም ሆኖ ግን ከሞላ ጎደል ሁሉም ክልሎች ለክልል መንግሥታት ተጠያቂ የሆነ ከፖሊስ ያለፈ "ልዩ ኃይል" ወይንም ሚሊሺያ በስፋት አቋቁመው እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል። መቼም እነኝህ ኃይሎች ከውጭ የሚመጣን ጠላት ለመመከት የቆሙ እንዳልሆኑም ግልጽ ነው።) ይህን ካመኑም ጤንነታቸው አጠያያቂ ነው የሚሆነው። ከዚህ ይልቅ የሚያምኑት የሚመስለው የራሳቸውን ማንነት ያንጸባርቃል ብለው የሚያምኑትን ክልል እስካገኙ ድረስ፤ ሌላው ሁሉ ይህን ጥያቄ አያነሳም የሚል ባዶ ተስፋ ወይንም ደግሞ "ካነሳም የራሱ ጉዳይ" እኔ የራሴን ይዤ በሰላም መኖር እችላለሁ የሚል ግዴለሽነት የተጠናወተው በፍጹም የተሳሳተ ግምት ሊሆን ይችላል።

አሁን ባለው ሕገ መንግሥት መሠረት ለምሳሌ የሲዳማን ጥያቄ መቀበልና ለመተግበር መሞከር፤ ችግሩን በፈጠረው መሳሪያ ላይ ተመርኩዞ ችግሩን ለመፍታት መሞከር የሚሆነውም ለዚህ ነው። የሲዳማ ጥያቄ የሲዳማ "የራስ እድል በራስ የመወሰን" ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ ባጠቃላይ ደቡብን፤ ቀስ እያለ ደግሞ ሁሉንም የሀገሪቱን "ብሄር፤ ብሄረሰብና ህዝቦችን" ስለዚህም ክልሎችን እንደገና መልሶ የማዋቀርን ጥያቄ ይዞ ስለሚመጣ ነው በቀላሉ ለመመለስ የሚያስቸግረው። ለዚህም ነው ገና የደኢሕዴን ማእከላዊ ምክር ቤት የሲዳማን ክልል የመሆን ጉዳይ እንደ ፓርቲ ተቀብያለሁ የሚል ውሳኔ ባስተላለፈ በጥቂት ቀናት ሌሎቹም ይህን ጥያቄ ያቀረቡ ዞኖች ይህንን የክልል ይገባኛል ጥያቄ ወዲያውኑ ባደባባይ ሰልፍ መጠየቅ የጀመሩት። ከላይ በፍኖተ ካርታው ላይ እንደተቀመጠው በሕገ መንግሥቱ ላይ የሰከነ ውይይት አድርጎ አጠቃላይ ሕገ መንግሥቱን የምንመለከትበት ሂደት ሳይኖር እነኝህን ከሕገ መንግሥት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች በዚህ የሽግግር ሂደት ለመፍታት የሚያስቸግረውም ለዚህ ነው። ቢያንስ በዚህ መልክ ሰላም፤ መረጋጋት ብሎም ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ከባድ ፈተና ነው የሚገጥመው። ከዚህም ባሻገር ግን ከምርጫው በፊት ሕገ መንግሥቱን ለመቀየር ቢሞከር በሕገመንግስቱ መሠረት ሕገ መንግሥቱን የመቀየርና የማሻሻል "ሕጋዊ መብት" የተሰጣቸው የክልል፤ የፌደራል ፓርላማም ሆነ የፌደሬሽን ምክር ቤት ያሉት አባላት በሙሉ በምንም ዓይነት ዴሞክራሲያዊ የምርጫ መስፈርት በሚያሟላ መልኩ ያልተመረጡና ስለዚህም የሕዝብን እውነተኛ ፍላጎት የሚያንጸባርቁ የሕዝብ ውክልና ያላቸው ኃይሎች አይደሉም። የለውጡ ኃይሎችም በውስጠ ታዋቂነት ሽግግሩን እንዲያካሂዱ የተሰጣቸው ማንዴት እስከምርጫው ድረስ የመንግሥትን የለት ተቀን ሥራ እንዲሠሩ እንዲሁም ለምርጫው ተዓማኒነት አስፈላጊ የሆኑትን የሕግና የተቋማት ሪፎርሞች አድርገው ሀገሪቱን በሰላማዊ መንገድ ወደ ምርጫው እንዲያደርሱና ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጠ አካል እንዲያስረክቡ ነው እንጂ እንደዚህ በጣም ዘላቂ እንድምታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ አይደለም።

## በሂደትና በጥልቅ እምነት መሀከል ያሉ ልዩነቶች

ግለሰቦች ወይንም የፖለቲካ ቡድኖች በነኝህ ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ያላቸው አመለካከት ወይንም የሚጠይቁት ጥያቄ ተገቢም ሆነ አልሆነ፤ የሚጠይቁትን ጥያቄ በምን መልክ ብንሄድ ልናገኘው እንችላለን ብለው የሚሄዱበት መንገድ ሌላ ራሱን የቻለ የግጭት ምክንያት መሆኑ እየታየ ነው። የደቡብ ክልል ገዢ ፓርቲ የሲዳማ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሲያስተላልፍ ሌሎች በክልሉ ያሉና የክልል ይገባናል ጥያቄ ያነሱት ዞኖች አደባባይ ለመውጣት ምክንያት አድርገው የሚሰጡት "እኛ የጠየቅነውን ጥያቄ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እየጠየቅን ባለንበት ሁኔታ" የክልሉ ፓርቲ ጉልበት፤ አመጽና ማስፈራራት የሚጠቀሙ ኢመደበኛ የወጣቶች አደረጃጀቶችን በመፍራት ነው ለሲዳማው ጥያቄ ቅድሚያ መልስ የሰጡት፤ በዚያ መልክ ከሆነ መልስ የሚሰጠው እኛም ወደ አመጽ መግባቱ ነው የሚያዋጣን" የሚል ግንዛቤ ቢይዙና ወደዚያ ዓይነት እንቅስቃሴ ቢገቡ ሊገርመን አይገባም። ባጠቃላይ ግን ከሕገ መንግሥት ጋር በተያያዘ የሚነሳው ጥያቄ ከሰላማዊ መንገድ ውጭ በጉልበትና በማስፈራራት ለመመለስ ሲሞከር ባጠቃላይ ጥያቄውን ዘላቂነት ባለው መልክ ለመፍታት ከማስቸገሩም ባሻገር የለውጡን ሂደት መጥፎ አጣብቂኝ ውስጥ ይከተዋል። ለምሳሌ የክልል እንሁንን ጥያቄ በአመጽና በማስፈራራት ማሳካት ይቻላል ተብሎ ከታመነ የዚህ ዓይነት አመጽ አንድ ብሄረሰብ ላይ ብቻ ተወስኖ ይቀራል ብለን ምናስብበት በቂ ምክንያት የለንም። ይህንንና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን (ዞኖች ክልል እንሁን፤ ወረዳዎች ዞን እንሁን፤ ቀበሌዎች ወረዳ ወይንም ዞን እንሁን፤ የዞኔ ወይንም የወረዳዬ ወሰን እኔ የምለው ነው...ወዘተ) ሁሉም በአመጽ አሳካለሁ ብሎ የሚያምን ከሆነ አገሪቱን ፍጹም የማያባራ የግጭት ቀጠና ሊያደርጋት ይችላል። ከሰላማዊ መንገድ ውጭ እነኝህን ጥያቄዎች ለመፍታት መሞከር ግን ሌላም መሠረታዊ የሆነ የመርህ ጥያቄ ይዞ ይመጣል። እነኝህ ጥያቄዎች በእውነትም የሚመለከተውን ማኅበረሰብ ነጻ ፍላጎት ባንጸባረቀ መልኩ መፈታት አለበት ብለን ካመንን፤ ከላይ በፍኖተ ካርታው በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጡት ጉዳዮች እውን ሳይሆኑ፤ ህዝብ ነጻ ፍላጎቱን ሊገልጽበት የሚችልባቸው የሰላም፤ የሕግና የተቋማት ለውጥ ሳይኖር፤ ሕዝበ ውሳኔ እንኳን ይደረግ ቢባል በርግጥ የህዝብ ፍላጎት ተንጸባርቋል ማለት ይቻላል? ጥያቄው በርግጥም የሕዝብ ጥያቄ ከሆነ በመጀመሪያ ማኅበረሰቡ ያሉት አማራጮች ከነሙሉ ምክንያታቸው ለሕዝቡ ቀርበው፤ ሕዝቡ ከቀረቡት አማራጭ ሀሳቦች ውስጥ ይበጀኛል የሚለውን በእውቀት ላይ ተመስርቶ ያለምንም ፍርሀትና መሸማቀቅ ወይንም አንዱን ከመረጥኩ ወደፊት በደህንነቴ ላይ ችግር የደርስብኛል ብሎ ሳይፈራ መምረጥ አለበት። ስለዚህም በመጀመሪያ በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች የሰላም ድባብ መስፈን አለበት። ምርጫውን በትክክል መግለጽ የሚችልበት አስፈጻሚ ተቋማትና አግባብ ያላቸው የሕግ መሻሻሎች መደረግ አለባቸው። ከዚህ ውጭ "የሕዝብ ፍላጎት" የሚባለው ጉዳይ በፖለቲካ ኃይሎች በኩል ለፕሮፓጋንዳነት የሚነዛ ካልሆነ በቀር በምንም ዓይነት የሕዝብ ፍላጎት መገለጫ ሊሆኑ አይችሉም። እነኝህን ጥያቄዎች ባግባቡ ለመመለስ ሌላም ግልጽ መሆን ያለበት ጥያቄ አለ። ከነኝህ ከሕገ መንግሥት ጋር በተያያዙ ጥያቄዎች ዙሪያ ህዝበ ውሳኔ (በየሚመለከተው የክልል እርከን) ይሰጥ ብንል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት የሚችለው ክፍል የትኛው የሕዝብ ክፍል ነው? የሚለው በጥንቃቄ መመለስ ያለበት፤ በዜግነትና በዘውጌ ማኅበረሰብ አባልነት መካከል ሕገ መንግሥቱ የሚሰጣቸውን መብቶች ተቃርኖ ውስጥ ሊከት የሚችል በጥንቃቄና በጥልቅ ውይይት በሀገር ደረጃ መመለስ ያሉብን ጉዳዮች ናቸው። ለምሳሌ በሀዋሳ ከተማ "ምንነት" ዙሪያ የሚወሰን ውሳኔ የሚመለከተው በከተማው

ውስጥ የሚኖረውን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው ወይንስ በዘውጌ ማንነቱ እየተሸነሸነ “ሲዳማው” ብቻ ነው በዚህ ከተማ ጉዳይ ውሳኔ መስጠት የሚችለው? ሁለተኛው ከሆነ ምን ያክል ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ይሆናል? ይህስ በዘላቂነት ከምናስበው የዜጎችን በነጻነት በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የመኖር መብት ጋር እንዴት እናቀናጀዋለን? እነኝህና መሰል ጥያቄዎችን ሁሉ በተረጋጋና ዘላቂነት ባለው መልኩ የምንፈታው አሁን ባለንበት ያልተረጋጋ ሁኔታ፤ ምርጫው ከመደረጉና የሕዝብ ወኪሎች ተገናኝተው ከመምከራቸው በፊት፤ በተለይም አመጽን ባጣቀሰ ሂደት ሊሆን በፍጹም አይችልም። ከዚያ በፊት የሚደረግ ሰላማዊ ያልሆነ እንቅስቃሴና እነኝህን እንቅስቃሴዎች ለመግታት በመንግሥት በኩል የሚወሰዱ እርምጃዎች ሁሉ የሰላም ድባቡን ይባሱኑ አበላሽቶ አጠቃላይ የለውጡን ሂደት ክፉኛ አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚከታቸው ዝም ብሎ በግምት ሳይሆን በተግባር እያየነው ያለነው የጊዜው ፈተናችን ሆኗል።

## ስለዚህ ምን ይደረግ? በምን መልክ ብንሄድባቸው ይሻላል?

ከዚህ አንጻር አሁን ለውጡን ከገጠሙት ፈተናዎች ውስጥ እጅግ የተወሳሰበ የሚመስለው ከዚህ ከሕገ መንግሥት ጋር የተቆራኙ ችግሮችን በሽግግሩ ሂደት የምንፈታበት መንገድ ነው። ባንድ በኩል ሕገ መንግሥቱ እንዳለ በሽግግሩም ሂደት ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚነት ያለው ዶኪመንት አድርጎ በማየት ማናቸውንም ጥያቄዎች በዚሁ መንገድ እየፈታን እንሄዳለን የሚለው አመለካከት የፈጠረው ግፊት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሕገ መንግሥት ቀድሞውንም ሙሉ ለሙሉ በሥራ ላይ ያልዋለና በእውነትም በሥራ ላይ ለማዋል በጣም አስቸጋሪ የሆኑ አንቀጾች ያሉት መሆኑና እነኝህ አንቀጾች በጋራ ስምምነት የምናሻሽልበት ሂደት ውስጥ ሳንገባ ጥያቄዎቹን ለመፍታት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑ የፈጠራቸው ተቃርኖዎች ናቸው። ሕገ መንግሥቱን በጋራ ስምምነት ለማሻሻል ደግሞ በመጀመሪያ የሰላም ድባብ በሀገሪቱ ሁሉ እንዲኖር ማድረግ፤ ቀጥሎም በትክክለኛ መንገድ የተመረጡ የሕዝብ ወኪሎች መኖራቸው አስፈላጊ በመሆኑ ምርጫው በአግባቡ እስከሚካሄድ ድረስና በሕዝብ ውይይትና ምክክር የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ ጊዜ የሚወስድና በትዕግሥት ሊጠበቅ የሚገባው መሆኑ ነው። ይህ ከሆነ በዚህ በሽግግር ወቅት ከሕገ መንግሥት ጋር የተያያዙትን ሁሉንም ጥያቄዎች ምርጫው እስከሚፈጸም ድረስና በሕዝብ ነጻ ፍላጎት የተመረጠና የሕዝብ ውክልና ያለው መንግሥት እስከሚመሰረት ድረስ ለጊዜው ማቆየትና ማኅበረሰቡ ሙሉ ትኩረቱን በመጪው ምርጫ ላይ አድርጎ ይህንን ምርጫ በፍጹም ከግጭቶች ነጻ የሆነ፤ በሰላማዊ መንገድ የሚደረግ፤ እርግጠኛ የሕዝብ ፍላጎት የሚንጸባረቅበት እንዲሆን ተግቶ የሚሠራበት ጊዜ ላይ ቢያውለው ይሻላል የሚል እምነት አለን።

በእምነታችን “ሕዝባዊነት” ላይ ጥርጣሬ አለን ማለት ነው። አቻኩለን የምንወስነው ውሳኔም እንደገና ነገ ለሌሎች ግጭቶች የሚዳርገን ከሆነ ችግሩን በመሠረታዊ መልኩ አልፈታነውም ማለት ነው።

እነኝህን ጥያቄዎች ዛሬውኑ አሁን ባለንበት የግርግር ሁኔታ ካልፈታነው የሚሉ ኃይሎች (ሀገሪቱ እንዳትረጋጋና ለውጡም ከዳር እንዳይደርስ ሆን ብለው ከሚፈልጉት ውጭ) ምናልባት የሚፈሩት እንደከዚህ በፊቱ አንድ ሕገ መንግሥት በጉልበት በስልጣን ላይ ባለው ኃይል ይጫንብናል ብለው ሊሆን ይችላል። ያ ከሆነ ደግሞ ይበልጥ ሊፈሩት የሚገባው የሕገ መንግሥቱን መቀየር ብቻ ሳይሆን ይህ ሁሉ የለውጥ ሂደት ያደርሰናል ብለን የምናስበው የዴሞክራሲያዊ

> **‹‹ሁሉም የራሱን አመለካከት የሕዝብ ፍላጎት ነጸብራቅ መሆኑን የሚያሳየው እምነቱ በሕዝብ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው። እሱ በከፍተኛ ስሜትና በእምነቱ እርግጠኛነት ቢያምንም ሌላው ሁሉ እንደሱ ያምናል ማለት እንዳልሆነ መቼም ያውቃል።››**

ከላይ የተጠቀሱት በሕገ መንግሥቱ ላይ ያሉት ልዩነቶች በመጨረሻ የሚፈቱት በሕዝብ ውሳኔ መሆኑ ላይ መቼም ክርክር የለም። ሁሉም የራሱን አመለካከት የሕዝብ ፍላጎት ነጸብራቅ መሆኑን የሚያሳየው እምነቱ በሕዝብ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው። እሱ በከፍተኛ ስሜትና በእምነቱ እርግጠኛነት ቢያምንም ሌላው ሁሉ እንደሱ ያምናል ማለት እንዳልሆነ መቼም ያውቃል። እምነቱን ግን በነጻነት አራምዶ፤ ማኅበረሰቡን አስተምሮ፤ የሚያምንበት እምነት የብዙሀኑ እምነት እንዲሆን መሥራት ይጠበቅበታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የሰላም ድባብ ሳይኖር ሊያደርገው አይችልም። ከዚያም በላይ እንደዚህ ዓይነት በጣም ስስ የሆኑ ጉዳዮች በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው በተረጋጋ መንገድ መወያየት ካልተቻለ አቀራራቢ መፍትሄ ማምጣትም አይቻልም። ጊዜ በመውሰዳችን የምናጣው ምንም ነገር የለም። ፍላጎታችን ምንም ሆነ ምን እነኝህ ጥያቄዎች መነሳታቸው፤ ቀጥሎም በሕዝብ ውሳኔ መፈታታቸው አይቀርም። ማኅበረሰቡ ተረጋግቶና ተወያይቶ የሚወስነውን ነገር ከፈራን በመጀመሪያውም ሥርዓት ግንባታ ራሱ ከሽፏል ማለት ነው። እሱ ከሆነ ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ምንም ሆነ ምን በተግባር ላይ ሊውል የማይችል ባዶ ወረቀት ነው የሚሆነው። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዴ መፍጠር ከቻልን ግን ይህን ሥርዓት የሚገዛውን ዋና ሕግ ከውይይትና ከሕዝብ ውሳኔ ውጭ ማንም ሊጭንብን እንዳይችል አድርገናል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነት ፍርሀት ያለባቸውን የኅበረተሰብ ክፍሎች ለማረጋጋትና በሕገ መንግሥቱ ላይ ያላቸውን አመለካከት በነጻነት የሚገልጹበትና ሀሳባቸው የበላይነት እንዲያገኝ ሕዝብ ሊያስተምሩበት የሚችሉበት ሰፊ እድል እንደሚኖራቸው እንዲያውቁት ለማድረግ ግን ይህን ለውጥ የሚመራውና ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያሸጋግረናል ብለን የምንጠብቀው መንግሥት የዚህን የሕገ መንግሥታዊ ውይይት ሂደት ከወዲሁ ለማኅበረሰቡ ግልጽ ቢያደርግ ከብዙ አላስፈላጊ ግጭት ያድነናል፤ የለውጡን ሂደትም ካደጋ ይጠብቀዋል ብለን እናምናለን። የፖለቲካ ኃይሎችና ማኅበረሰቡም በለት ተቀን ግጭቶች ላይ ቀልቡን ከሚጥል ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ በሆነው በመጪው ምርጫ ላይ እንዲያተኩርና እንዲዘጋጅ ይረዳዋል።

# ኢዜማ ቀጣዩን ምርጫ ለማሸነፍ በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑ ተገለፀ።

ታኅሣሥ 2 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ ምርጫ ወረዳዎች ቀጣዩን ሀገር አቀፍ ምርጫን ለማሸነፍ ወረዳዎቹ የሚጠበቅባቸው የአቅም ደረጃ ላይ ለማድረስ ሥራ እየሠራ መሆኑ ተገለፀ፡፡

ኢዜማ ባሳለፈነው ሳምንት ኅዳር 27 እና ኅዳር 28 ቀን 2012 ዓ.ም አዳማን፣ ሀዋሳ፣ ዲላ እንዲሁም አዶላን ከተማ ጨምሮ በ26 ዞኖች በ264 ምርጫ ወረዳዎች ለሚገኙ አባላት ስልጠና መስጠቱን እና የምዘና ሥራ መሥራቱን የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ኢዜማ ምርጫውን ለማሸነፍ ማድረግ የሚገባውን ተግባራትና ዝግጅት ለአባላቱ ማስረዳት፤ በኢዜማ የተዘረጉት መዋቅሮችን ምርጫን የማሸነፍ አቅማቸው ምን ደረጃ እንዳለ ግምገማ ማካሄድ እና የምርጫ ወረዳዎቹን ያላቸውን ብቃት መፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ስልጠናው የተሰጣቸው አባሎችና አመራሮች ወደተለያዩ ምርጫ ወረዳዎች በመውረድ በድርጅት ጉዳይ በኩል የተዘጋጁትን ቅጾች መሠረት በማድረግ ምርጫ ወረዳዎች ላይ ምዘና በማካሄድ ውጤቱ ከታየ በኃላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ፤ እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ለማሸነፍ ብቁ ያልሆኑ ምርጫ ወረዳዎችን ተጨማሪ የማብቃት ሥራ ለመሥራት ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ አባላቱም ስልጠናው መሰጠቱ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉ ምርጫውን ለማሸነፍ እንደሚረዳ ከማዕከልም ክትትልም ሊኖር እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ኢዜማ አሁን እየሰራቸው ያሉ ሥራዎች ሰፋፊና አድካሚም ቢሆኑም ያለውን አቅም ተጠቅሞ ምርጫውን ለማሸነፍ በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገልጸዋል፡፡

# ኢዜማ የገቢ ማሰባሰቢያ ሊያካሄድ ነው

ታሕሳስ 02/2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የፊታችን እሁድ ታሕሳስ 5 ቀን 2012 ዓ.ም በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ማዘጋጀቱን የኢዜማ የግብአትና የሀብት አሰባሳቢ ኮሚቴ አባል የሆኑት አንድነት ሽፈራው ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ታሕሳስ 5 ቀን 2012 ዓ.ም በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በሚካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም የኢዜማን እንቅስቃሴ ለመደገፍ የሚያስችሉ የቁሳቁስ፣ የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ይገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ አንድነት ሽፈራው አስረድተዋል፡፡ ለኢዜማ ድጋፍ ማድረግ የሚፈልጉ አካላት ድጋፋቸውን እንዴትና በምን መልኩ ድጋፍ ማድረግ እንደሚችሉ ለመግለፅና ለፓርቲው እንቅስቃሴ ሊያግዙ የሚችሉ የግብአትና የቁሳቁስ ድጋፍ ለማሰባሰቢ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሙን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን የኮሚቴው አባል ገልፀዋል፡፡ የግብአትና የሀብት አሰባሳቢ ኮሚቴው በእለቱ በሚኖረው የገቢ ማሰባሰቢያ ከ2 እስከ 3 ሚሊየን ብር አገኛለሁ ብሎ እንደሚጠብቅም አያይዘው ገልፀዋል፡፡

በኢንተርኮንቲኔንታል በሚካሄደው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም የራት ግብዣን የሚያካትት ሲሆን ከራት ግብዣው በተጨማሪ ዲስኩር፣ ግጥምና ባንድ እንዲሁም ጨረታ እንደሚኖር ከወጣው መርሃግብር ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሀብትና ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴው ዝርዝር ጉዳዮችን ለማብራራት ሐሙስ ታህሳስ 02 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል ጋዜጣዊ መግለጫ የሚሰጥ ይሆናል፡፡